# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
# ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL

ኢሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው::
**EHRCO** stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.

## 100ኛ ልዩ መግለጫ

## አጥፊዎች ለፍርድ መቅረባቸው በጎ ድርጊት ነው!

ሚያዚያ 22 ቀን 1999 ዓ.ም

**መግቢያ**

ለዘመናት የዘለቀውን ተቻችሎ የመኖር አኩሪ ባህላችንን የሚያናጉ ተደጋጋሚ የጎሳ ግጭቶች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ተከስተው ከፍተኛ ጥፋት መድረሱ ይታወቃል:: በቅርቡ ደግሞ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በኢሉባቦር፣ በጂማ እና በምዕራብ ወለጋ ዞኖች በተፈጠሩ የሀይማኖት ግጭቶች ሰላማዊ ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል፤ በሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ተፈናቅለዋል፤ አብያተክርስቲያናት ተቃጥለዋል፤ ከፍተኛ የንብረት ውድመትም ደርሷል:: በጎሳና በሀይማኖት ሽፋን ወንጀል በማራመድ ከላይ የተገለጹት ጉዳቶች እንዲደርሱ ያደረጉ ግለሰቦች ለፍርድ አለመቅረባቸው ለችግሩ መባባስ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ግልጽ ነው::

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በተለያዩ ጊዜያት የተከሰቱ የጎሳ ግጭቶችን፣ እንዲሁም በቅርቡ የተከሰተውን የሀይማኖት ግጭት አስመልክቶ ባወጣቸው መግለጫዎች ተጠያቂዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ ጉዳት የደረሰባቸው ተገቢ ካሳ እንዲሰጣቸውና፣ ግጭቶቹ እንዳይደገሙ ዘላቂ መፍትሄ እንዲፈለግላቸው ማሳሰቡ ይታወቃል::

ኢሰመጉ በዚህ 100ኛ መግለጫዉ ከላይ ለተጠቀሰው የሀይማኖት ግጭት ተጠያቂ የሆኑት ግለሰቦች ለፍርድ በመቅረባቸው እንዲሁም በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጌዲኦ ዞን መጋቢት 28 ቀን 1998 ዓ.ም ተፈጥሮ በነበረው ግጭት ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች በከፊልም ቢሆን የማቋቋሚያ ገንዘብ በክልሉ መንግስት መሰጠቱ በጎ እርምጃ መሆኑን በመግለጽ መንግስት ተጨማሪ እርምጃዎችን እንዲወስድ ይጠይቃል::

## ዝርዝር

### ሀ. በኦሮሚያ ክልል ለተከሰተው የሀይማኖት ግጭት ተጠያቂዎች ለፍርድ መቅረብ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በኢሉባቦር፣በጂማ እና በምዕራብ ወለጋ ዞኖች በሚገኙ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስርዓት መሰረት መስከረም 16 ቀን 1999 ዓም የመስቀል ደመራ በዓልን ለማክበር በየአጥቢያቸው በተሰበሰቡ የእምነቱ

ተከታዮችና የአካባቢው ነዋሪዎች ላይ በቡድን በተደራጁ የእስልምና ተከታዮች በተሰነዘረ ጥቃት የህይወት መጥፋት፣ የአካል ጉዳትና ከፍተኛ የንብረት ውድመት እንደደረሰና የማምለኪያ ቦታዎቹም መቃጠላቸውን እንዲሁም በርከታ ሰዎች ለስደት መዳረጋቸውን ኢሰመጉ በስፍራው ተገኝቶ ከአካባቢው ባሰባሰበው ማስረጃ አረጋግጦ ዝርዝሩን በ97ኛ ልዩ መግለጫው ማውጣቱ ይታወሳል:: በዚሁ መግለጫ እንደተመለከተው ከመስከረም 16 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 4 ቀን 1999 ዓ.ም ባሉት ቀናት ውስጥ ከላይ በተጠቀሱት ዞኖች ውስጥ በርካታ ዘግናኝ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተፈጽመዋል:: ኢሰመጉ በዚሁ መግለጫው ለተከሰተው ግጭት ተጠያቂ የሆኑ ግለሰቦች ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ ተጎጂዎች ዘላቂ የሆነ የህይወትና የንብረት ዋስትና እንዲሰጣቸው፣ እንዲሁም ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው የሚገኙትም መልሰው እንዲቋቋሙና ተገቢው እርዳታ እንዲደረግላቸው ጠይቋል::

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በወቅቱ ለተፈፀሙት ወንጀሎች ተጠያቂዎችን ተከታትሎ ለፍርድ በማቅረብ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥር 16 ቀን 1999 ዓም በዋለው ችሎት 04790 በሆነ የመዝገብ ቁጥር ከቀረቡት 129 ተከሳሾች ውስጥ በ69ኙ ላይ እንደጥፋታቸው ክብደትና ቅለት ከገንዘብ አንስቶ እስከ ሞት የሚደርስ የቅጣት ውሳኔ አስተላልፏል:: የቅጣት ዓላማው ለአጥፊዎቹ ትምህርት ለሌሎች ሰዎች ደግሞ ማስጠንቀቂያና ማስተማሪያ እንደመሆኑ መጠን በመንግስት የተወሰደው እርምጃ በክልሉም ሆነ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች እና የተለያዩ እምነት ተከታዮች መኖሪያ በሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደዚህ አይነት ልዩነትን መሰረት ያደረገ ጭፍጨፋ ዳግም እንዳይከሰት በማድረግ ረገድ ከፍ ያለ ድርሻ ይኖረዋል:: ስለሆንም ኢሰመጉ የሞት ቀጣትን በማናቸውም መልኩ የሚቃወም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ መንግስት ጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት አፋጣኝ ውሳኔ ማግኘቱን ግን አዎንታዊ እርምጃ አድርጎ ይመለከተዋል::

ሆኖም ቀደም ብሎ መከላከልና ለዜጎች አስተማማኝ ደህንነትን ማረጋገጡ አማራጭ የሌለው ጉዳይ በመሆኑ ለዚህም መንግስት ትኩረት እንዲሰጥና ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ባለው ሁኔታ በአንዳንድ ክልሎች ለታዩትና እየታዩ ለሚገኙት የኀሳ ግጭቶች እጃቸው ያለበትን ሰዎች ህግ ፊት እንዲቀርቡ ኢሰመጉ በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ይጠይቃል::

## ለ. በጌዲኦ ዞን በጎሳ ግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ የመልሶ ማቋቋም መደረጉ

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጌዲኦ ዞን በይርጋ ጨፌ፣ በፍስሃ ገነት፣ በዲላ፣ በቡሌ፣ እና በጨለለቅቱ ከተሞች ውስጥ ነዋሪ በሆኑ የጌዲኦ ብሄር ተወላጆችና በሌሎች ብሄር ተወላጆች መካከል መጋቢት 28 ቀን 1998 ዓ.ም ተፈጥሮ በነበረው ግጭት በህይወትና በንብረት ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን ዝርዝር ኢሰመጉ በ25ኛው መደበኛ መግለጫው ማውጣቱ ይታወሳል:: ኢሰመጉ በዚሁ መግለጫው ለግጭቱ ተጠያቂ የሆኑት ግለሰቦች ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ካሳ እንዲከፈላቸዉና ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ እንዲፈለግለት አሳስቦ ነበር::

የጉዳቱ ሰለባዎች ከሆኑት የአምስት ከተሞች ህዝቦች መካከል በቡሌ ከተማ የጉዳት ሰለባ ለሆኑት ግለሰቦች በክልሉ መንግስት የመልሶ ማቋቋም ስራ መሰራቱን ኢሰመጉ እንደበጎ ተግባር የሚያየው ሆኖ በቀሪዎቹ አራት ከተሞች ለሚኖሩ ተጎጂዎችም ትኩረት እንዲሰጥ ኢሰመጉ በድጋሚ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

እንዲሁም ከፍተኛ ሰብአዊና ቁሳዊ ጥፋት ያደረሱት ግለሰቦች ለፍርድ አለመቅረባቸው መሰረታዊ የፍትህ መጓደል ከመሆኑም በተጨማሪ በግጭቱ ጉዳት በደረሰባቸው ግለሰቦች የወደፊት ኑሯቸው ላይ ዋስትና እንደሚያሳጣቸው የግጭቱ ተጎጂዎች ለኢሰመጉ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት የፈጸሙትን ግለሰቦች ለፍርድ በማቅረብ በህገ-መንግስቱ የተጣለበትን የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ሀላፊነት እንዲወጣ ኢሰመጉ በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ይጠይቃል፡፡

## ማጠቃለያ

- ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከተው የሰብአዊ መብት ጥሰት የፈጸሙትን ግለሰቦች ለፍርድ ማቅረብ መሰረታዊ የፍትህ ጥያቄ ከመሆኑም በተጨማሪ ተመሳሳይ ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ ትምህርት የሚሰጥ በመሆኑ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በሀይማኖት ሽፋን ወንጀሉን የፈጸሙትን ተከታትሎ ለፍርድ ማቅረቡ የሚበረታታ ተግባር ነው፡፡
- የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስትም ጌዲኦ ዞን በይርጋ ጨፌ፣ በፍስሃ ገነት፣ በዲላ፣ በቡሌ፣ እና በጨለለቅቱ ከተሞች ውስጥ መጋቢት 28 ቀን 1998 ዓ.ም ተፈጥሮ በነበረው ግጭት በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሱት አጥፊዎች ላይ ተገቢ ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድና ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም በሚደረገው ጥረትም ለሁሉም ተጎጂዎች ትኩረት እንዲሰጥ ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡

በተጨማሪም ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለሕግ ልዕልና የቆማችሁ ዜጎች፣ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የመንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች የኢትዮጵያ መንግስት በአገሪቱ ህገ-መንግስት የተረጋገጡትን ሰብአዊ መብቶች እንዲያከብርና እንዲያስከብር በሚከተሉት አድራሻዎች በመፃፍና በመደወል የበኩላችሁን ግፊት ታደርጉ ዘንድ ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡

- **ክቡር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ**
  *የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ-ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0900*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ደግፌ ቡላ**
  *የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ-ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0722*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ**
  *የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-11) 155 2020*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ**
  *የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-11) 155 2020*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ሲራጅ ፈርጌሣ**
  *የኢፌዲሪ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0000*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ አሰፋ ከሲቶ**
  *የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0874*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር ዶ/ር መሐመድ ያሲን**
  *የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 101769፣ ፋክስ (251-11) 551 3642*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ፍቅሩ ኛካል**
  *የደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 18፣ ፋክስ (251-46) 220 1950*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አምባሳደር ካሣ ገ/ሕይወት**
  *የኢፌዲሪ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1165፣ ፋክስ (251-11) 645 9290*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ አባይ ተክሌ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ዋና እምባ ጠባቂ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 2459፣ ፋክስ (251-11) 645 9229*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*